**ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን**
**ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) የአጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 234/2013 መሠረት የወረቀትና የወረቀት ወጠፆች እና የኬሚካል አምራች ኢንዱስትሪዎች ማሟላት የሚገባቸውን የተጨማሪ እሴት ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ የመመሪያው ማሻሻያ ከጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲደረግ እያሳሰብን ማሻሻያውን ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ በስራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ

ጋር

ግልባጭ

ለግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር</u>

**የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሀለተኛ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ**
**ቁጥር 234/2013ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 262/2013 (2)**

የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሀለተኛ ሚደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 234/2013 ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሀለተኛ ሚደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 234/2013ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 262/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሀለተኛ ሚደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 1**

በየኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ሊታከል የሚገባ የተጨማሪ እሴት ምጣኔ

| የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ | የተጨማሪ እሴት መጣኔ % |
|---|---|
| 7. የወረቀት፣ የወረቀቶች ምርቶች እና የህትመት ሥራዎች አምራች | |
| 7.1 የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች አምራች | |
| 7.1.1 የወረቀት አምራች ኢንዱስትሪዎች | 20 |
| 7.1.2 የካርቶንና የወረቀት ማሸጊያ (ፓኬጂንግ) አምራች ኢንዱስትሪዎች | 21 |
| 7.1.3 የወረቀት የንፅህና ማጠበቂያ አምራች ኢንዱስትሪዎች | 18 |
| 7.1.4 የወረቀት ኮንቨርቲንግ ኢንዱስትሪ | 22 |
| 8. የኬሚካል እና የኬሚካል ወጠፀች አምራች | |
| 8.1 የአስፋልት አምራች | 20 |

3. **<u>ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን</u>**

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 28 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ህዳር ____________ ቀን 2010 ዓ.ም*

*አብርሃም ተከስተ (ዶ/ር)*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር*
*ሚኒስትር*